የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ
የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ
ኦዲት ሪፖርት

ህዳር /2014 ዓ.ም

አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ ዲያስፖራኤጀንሲ

የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት ሪፖርት

የኢትዮጵያ ዲያስፖራ ኤጀንሲ የተመደበለትን የመደበኛ ሂሳብ በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፣ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግሥት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት መያዙንና የመንግሥት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው::

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ስልጣንና ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሠረት በማድረግና የዋና ኦዲተርን የኦዲት ስልት በመከተል ነው፡፡

እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ (የኦዲት አስተያየት) ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት ኤጀንሲው ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች ፤ መዛግብት፤ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በኤጀንሲው ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው ፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው፡፡

የሚከተሉት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል፡፡

- የገቢ/የዕርዳታ/የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በትክክል የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው

ገቢ፤ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

ወጪ፤

1. በፌዴራል መንግስት የግዥ አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ቢያንስ ከ3 አቅራቢዎች የዋጋ ማወዳደሪያ በመሰብሰብ እና በማወዳደር አሸናፊ ከሆነው ድርጅት ግዥ መፈፀም ሲገባው ከመመሪያ ውጭ በቀጥታ ለተፈፀመ የአገልግሎት ግዥ በድምሩ ብር 151,925.42 ተከፍሎ ተገኝቷል።
2. በፌዴራል መንግስት የግዥና ንብረት አስተዳደር መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15/2 እና 15/3 መሰረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸው ቢገልጽም፤ አቅራቢዎች ሳይወዳደሩ በቀጥታ የአገልግሎት ግዥ ለተፈፀመበት ብር 469,686.28 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል።
3. የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 ቁጥር 14/4 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መሟላት እንዳለበት ያዛል። ነገር ግን በኢንቮይስ ቁጥር 1956 በቀን 29/10/13 በሂሳብ መደብ 2241106 (6256) በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ በወጪ ከሚታየው ብር 134,906.81 ውስጥ በዱባይ ኤምባሲ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 000328 ለብር 24,957.00 የቀረበው ማስረጃ ትክክለኛና ህጋዊ መሆኑን ማረጋገጥ አልተቻለም።
4. የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 8(2/ለ) ወጪ ከመፈፀሙ በፊት ስለ ወጪው የተሟላ ማስረጃ መቅረብ እንደሚገባ ያዛል። ነገር ግን በተለያዩ ቀናትና የወጪ ማስመሰከሪያዎች በድምሩ ብር 53,648.21 የወጪ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያ ተፈፅሞ ተገኝቷል።

ተሰብሳቢ ሂሳብ፤

5. የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እንዲሁም የፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ቅድሚያ ክፍያዎች በወቅቱ እንዲወራረዱ ቢያዝም፤ በኤጀንሲው የሰኔ 30/2013 የሂሳብ ሪፖርት በተለያዩ የሂሳብ መደቦች በድምሩ ብር 94,452,513.87 በተሰብሳቢ ተይዞ የቆየ ሲሆን፤ በሂሳብ መደብ 5217109 (4210) ብር 93,010,204.16 ለ36 በውጪ ሀገራት ለሚገኙ ኢንባሲዎችና ቆንጽላ ጽ/ቤቶች የተላከ ሲሆን ስራ ላይ የዋለው ማስረጃው ቀርቦ መወራረድ ሲገባው ያልተወራረደ፣ ያልተሰራበት ደግሞ ገንዘቡ ለኤጀንሲው ተመላሽ ያልተደረገ፤ በሂሳብ መደብ 5217112/አዲስ/ ብር 170,997.84 እንዲሁም በሂሳብ መደብ 5217205/4253/ የተያዘ ብር 467,966.25 ያልተወራረደ መሆኑን፤ በሂሳብ መደብ

5217302/4202/ የተያዘ የጥሬ ገንዘብ ጉድለት ብር 75,345.62 ከሚመለከተው አካል ገቢ ሳይደረግ የቆየ በድምሩ ብር **93,724,513.87** በወቅቱ ያልተወራረደ የተሰብሳቢ ሂሳብ ተገኝቷል፡፡

ከላይ ከተራ ቁጥር 1 እስከ 5 በተገለጹት ጉልህና መሠረታዊ ልዩነቶች የተነሳ በእኛ አስተያየት የኤጀንሲው የሂሳብ ሪፖርቶች ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም. የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት በአጥጋቢ ሁኔታ አያሳዩም፡፡

<u>ትኩረት የሚያሻቸው ጉዳዮች፤</u>

ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

6. የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 መሰረት በትክክለኛ የሒሳብ መደብ መመዝገባቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ **ብር 749,984.11** የተከፈለባቸው ወጪዎች በመመሪያው መሠረት በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት መደረጋቸው ታውቋል፡፡
7. በተለያዩ ቀናትና የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ ብር 819,568.97 ለተገዙ ንብረቶች የተከፈለ ሲሆን፣ ዕቃዎቹ በንብረት ገቢ ደረሰኝ (ሞ-19) ገቢ ሳይደረጉ ሂሳቡ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

<u>በጀት፤</u>

8. ለኤጀንሲው በበጀት ዓመቱ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከተመደበው መደበኛ በጀት ብር 122,432,153.00 ከ10% በላይ በየሂሳብ መደቦቹ ብር 83,706,611.11 (68.37%) ያልተሰራበት በጀት መሆኑ ታውቋል፡፡
9. የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል አራት ተራ ቁጥር 13 የበጀት ዝውውር ስልጣን ውክልና ሚኒስቴሩ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ 24(2) መሰረት የተሰጠውን የበጀት ዝውውር ስልጣን በውክልና ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች መሆን እንደሚገባ እና በተራ ቁጥር 18 ላይ ዉክልና የተሰጠው የበላይ ኃላፊው በሚወክለው ሰው የበጀት ዝውውሩ ቅጽ በትክክልና በበቂ ኮፒዎች መሞላቱን ካረጋገጠ በኋላ ስለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚለው ክፍት ቦታ ላይ መፈረም እንደሚችል ይገልጻል ይሁን እንጂ

በድምሩ ብር 7,050,000.00 ያለ ውክልና በከፍተኛ የዕቅድ ዝግጅት ግምገማ ባለሙያ ተከናውኖ ተገኝቷል፤

10.በተጨማሪ በዚሁ መመሪያ ተራ ቁጥር 2 ላይ ከአንድ ዋና የሂሳብ መደብ ወደ ሌላ ዋና የሂሳብ መደብ ከ6400/ለድጋፍና ለመዋጮ /ከተፈቀደው በጀት ወደ ሌላ እንዲሁም ከ 6100 /ከደመወዝና አበል /ወደ 6200 /ስራ ማስኬጃ /በጀት ማዛወር በሚፈለግበት ጊዜ የበጀት ዝውውር ጥያቄን ለሚኒስቴሩ ቀርቦ መፈቀድ እንዳለበት ያዛል ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በከፍተኛ የዕቅድ ዝግጅት ግምገማ ባለሙያ ከመመሪያው ውጪ የብር 3,600,000.00 ለገንዘብ ሚንስቴር ሳይቀርብ ዝውውር የተፈጸመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

<u>ሌሎች ጉዳዮች፤</u>

11. <u>ንብረት፤</u>

- ሲሪያል ቁጥር ያላቸው ንብረቶች ተገዝተው በሞዴል 19 (የንብረት ገቢ ደረሰኝ) እንዲሁም በሞዴል22 (የንብረት ወጪ ደረሰኝ) ተጠይቆ በሁለቱም ገቢም ሆነ ወጪ ሲደረጉ የተመረተበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) የማይመዘገብ መሆኑ፤

- በክፍል 3 የስቶክ አስተዳደር ስርአት ተራ ቁጥር 10 ሀ የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሰራተኛ መሰጠት እንደሌለባቸው ያዛል የሁን እንጂ በኤጀንሲው የንብረት ክፍል መዝጋቢ እና የንብረት ጠባቂ ያልተለየ እና በአንድ ሰው ብቻ የሚፈጸም መሆኑን፤

- በክፍል 3 የስቶክ አስተዳደር ስርአት ተራ ቁጥር 9 የስቶክ ቁጥትር ስርአቶች ተራ ቁ.2/ሐ ንብረት ገቢ ወይም ወጪ ከተደረገባቸው በኋላ በተቻለ ፍጥነት ዋናው የስቶክ መዛግብቶች ላይ ማሻሻያ መደረግ እንዳለበት ያዛል ነገር ግን በ/መ/ቤቱ የስቶክ ካርድ በአገልግሎት ላይ አለመዋሉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከሠላምታ ጋር

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ
የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ኦዲት
የሥራ አመራር ሪፖርት

መግቢያ

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 ለመስሪያ ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ የ2013 በጀት ዓመት ሂሣብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ ሂሳቡን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሪፖርቱ አላማ

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙ የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶችን የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢው የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ለማድረግ ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን መሰረት በማድረግ እና የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን የኦዲት ሥልት በመከተል ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመስራት ኤጀንሲው ባዘጋጀው የሂሳብ ሪፖርት ላይ አጥጋቢ የሆነ ማረጋገጫ /የኦዲት አስተያየት/ ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን የሚያካትተው፡-

- በሂሳብ ሪፖርቶቹ ላይ የሰፈሩት አሀዞችና ሪፖርቶቹን የሚደግፉ ማስረጃዎች በናሙና መመርመር፣
- የኤጀንሲውን ሥራ አመራር የሂሳብ ሪፖርቶቹን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎቹ ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የሂሳብ ሪፖርቶቹ አግባብነት ያላቸውን አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና መመርመርን ይጨምራል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹ ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆናቸው በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል፡፡ የኦዲት

አስተያየት ላይ ለመድረስ በሂሳብ ሪፖርቶቹ ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡

በዚህ ሪፖርት ከተመለከቱት የአሰራርም ሆነ የሂሳብ አያያዝ ድክመቶች በተጨማሪ ሌሎች ድክመቶች ወይም ስህተቶች ሊኖሩ የሚችሉ በመሆኑ የሂሳብ ሪፖርቶቹን ለማዘጋጀት የተዘረጉትን የውስጥ ቁጥጥሮችና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶቹን የማዘጋጀት ኃላፊነት የኤጀንሲው ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶቹን ኦዲት ማድረግና ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው፡፡

የኢትዮጵያ ዳያስፖራ ኤጀንሲ

የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት

ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

የኤጀንሲው የ2013 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶች ቀጥሎ ቀርበዋል፡፡

1. የወጪ ሂሳብ፤

1.1 ግኝት፤ በዋጋ ማወዳደሪያ መግዛት ሲገባቸው በቀጥታ ለተፈጸሙ ግዥዎች የተከፈለ ብር 151,925.42፤

የፌዴራል መንግሥት የግዥ እና ንብረት አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 649/2001 አንቀፅ 51 ንኡስ አንቀጽ 1/ሀ የመንግስት መ/ቤቶች ከአንድ አቅራቢ ግዥ መፈጸም የሚችሉት እቃው ወይም አገልግሎቱ የሚገኘው ከአንድ እጩ ተወዳዳሪ ብቻ በመሆኑ ምክንያት ማወዳደር የማይቻል መሆኑ ሲረጋገጥ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በመመሪያው መሠረት ግዥ የፈጸመ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ ቢያንስ ከ3 አቅራቢዎች የዋጋ ማቅረቢያ ተሰብስቦ አሸናፊ ከሆነው ድርጅት ግዥ መፈፀም ሲገባው ግዥዎች ከመመሪያ ውጭ በቀጥታ ለተፈፀመ የአገልገሎት ግዥ በድምሩ ብር 151,925.42 ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስጋት

- መመሪያዎችን ያልተከተሉ ግዥዎች ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡
- ፍትሐዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡
- መንግስት ሊያገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ለኦሞካር የመኪና ኪራይ ብር 103,409.96 ክፍያን በሚመለከት ውጭ ጉዳይ ሚ/ር የተጫረቱበት ሰነድ እና ዲያስፖራ የተዋዋለበት ውል የቀረበልን ሲሆን ነገር ግን የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር በተጫረተበት ውል መግባታቸው አግባብ ሆኖ አላገኘነውም፡፡

የኢንተር ኮንቴነንታል የሆቴል አገልግሎት ግዥውን በሚመለከት እንግዶቹ ቀድመው ሆቴሉን በመያዛቸው የተደረገ እንደሆነ በሰነዱ ላይ የተገለጸ በመሆኑ የተሰጠው ምክንያት አልተቀበልነውም በመሆኑም ተገቢውን ውድድር በማድረግና ውል አስቀድሞ በመያዝ አገልግሎቶቹ ሲፈለጉ ሆቴሎቹ አገልግሎቶቹን እንዲያቀርቡ ሊደረግ ይገባል ፡፡

ግራፊክ ዲዛይንን በሚመለከት በዚህ ዘርፍ የተሰማሩ ድርጅቶችን ከአቅራቢ ዝርዝር ውስጥ በመለየት ውድድር ሊከናወን ይገባል፡፡

ከሰርቨር ጋር በተያያዘ ዲያስፖራ ኤጀንሲ የውጭ ጉዳይ ሚንስቴር ለራሱ ስራ በመረጠው አቅራቢ ሊፈጸም አይገባም፡፡ በመሆኑም በፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ግዥው አቅራቢዎችን በማወዳደር ሊፈጸሙ ይገባል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

- ብር 103,409.96 የጨረታ ሠነዱ ከውጩ ጉዳይ ሚኒስቴር ይገኛል አቅርበናል፡፡
- ብር 13,245.56 አዋጅ አንቀጽ 51 ንዑስ አንቀጽ 1(ረ) መሠረት
- ብር 15,000 በማኔጅመንት ውሳኔ መሠረት ግዥ የተፈጸመ መሆኑ
- ብር 20,269.90 ቀደም ሲል በውጪ ጉዳይ ሚኒስቴር ሰርቨሩን የሚጭን ባለሙያ በመሆኑ፤

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.2 ግኝት፤ <u>ጨረታ ሳይወጣ በቀጥታ ለተፈጸመ ግዥ የተከፈለ በድምሩ ብር 469,686.28</u>

በፌዴራል መንግሰት የግዥ ንብረት አስተዳደር መመሪያ ክፍል 4 አንቀጽ 15/2 እና 15/3 መሰረት በአዋጁና በመመሪያው በተፈቀደው ሁኔታ ካልሆነ በስተቀር የመንግስት መ/ቤቶች ማናቸውንም ግዥ በግልጽ የጨረታ ዘዴ መፈጸም እንዳለባቸውና ከዚህ ውጭ በሌሎች የግዥ ዘዴዎች ግዥ መፈጸም የሚችሉት በአዋጁና በመመሪያው የተገለጹት ሁኔታዎች ሲሟሉ ብቻ እንደሆነ ይገልጻል፡፡ በመሆኑም መምሪያው የሚያከናውናቸው ግዥዎች በግዥ አዋጅና መመሪያ መሠረት መሆኑ ሲጣራ፣ ፡፡ መ/ቤቱ ካለምንም የማወዳደሪያ ዘዴ በቀጥታ የአገልግሎት ግዥ በብር 469,686.28 የተገዛ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል፡፡

<u>ስጋት</u>

- መመሪያዎችን ያልተከተሉ ግዥዎች ሊፈጸሙ ይችላሉ፡፡
- ፍትሐዊ የገበያ ውድድር እንዳይኖር ሊያደርግ ይችላል፡፡
- መንግስት ሊያገኝ የሚችለውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ሊያሳጣ ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>

ሂልተን ሆቴል መንግስታዊ ድርጅትም ቢሆንም ፍትሃዊ ውድድር ለማስፈን መወዳደር ስለሚኖርበት አልተቀበልነውም፡፡ በመሆኑም በፌዴራል መንግስት የግዥ መመሪያ መሰረት ግዥው አቅራቢዎችን በማወዳደር ወይም አስገዳጅ ምክንያቶች ካጋጠሙ በሚመለከተው አካል በማስፈቀድና የግዥ መመሪያውን በተከተለ መልኩ መፈፀም ይኖርበታል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

ብር 469,686.28 በተመለከተ ሂልተን ሆቴል መንግስታዊ ተቋም በመሆኑና በፓኬጅ ውል በመግባት የተፈጸመ ነው፤

የኦዲተር አስተያየት

በተሰጠው የኦዲት ማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ሊከናወን ይገባል፡፡

1.3 ግኝት፤-በተገቢው የሂሣብ መደብ ያልተመዘገበ የወጪ ሂሳብ ብር 749,984.11

የፌዴራል መንግሥት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ዓ.ም. በክፍል ሁለት አንቀፅ 6 ተራ ቁጥር 4 ላይ የመንግስት መስሪያ ቤቶች በበጀት አደረጃጀት ሥርዓት መሠረት የተፈቀደላቸው በጀትና የወጣውን ወጪ በሚያሳይ መልኩ ተለይቶ በተሰጠ የበጀት መለያ መደብ ተጠቅመው የሂሳብ እንቅስቃሴያቸውን መመዝገብ እንዳለባቸው ይገልጻል:: ይሁን እንጂ የመ/ቤቱ የወጪ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤ በተለያዩ የወጪ ማስመስከሪያዎች በድምሩ **ብር** 749,984.11 የተከፈለባቸው ወጪዎች በመመሪያው መሠረት በተገቢው የሂሳብ መደብ ሳይመዘገቡ በወጪ ሂሳብ ሪፖርት መደረጋቸው ታውቋል፡፡

ስጋት

- ወጪዎች በተገቢው የወጪ ሂሳብ መደብ ተመዝግበው ሪፖርት ካልተደረጉ የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርት ትክክለኛ ገፅታ ላያሳይ ይችላል፡፡
- የሂሳብ አያያዙ የበጀት አጠቃቀም ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ያሳድራል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ፤

የፍጥነት መቆጣጠሪያ ግዥን በሚመለከት የተሰጠው ምላሽ ግልጽ አይደለም ፡፡ በቀሪዎቹ ግኝቶች ላይ ኤጀንሲው የፌዴራል መንግስት የሂሳብ አወቃቀር ስርዓትን ተከትለው በተገቢው የሂሣብ መደብ እንዲመዘገቡ ተገቢው ቁጥጥር ሊደረግ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

- በሲስተም ምዝገባ ችግር የተፈጠረ በመሆኑ የህትመት ምዝገባው በትምህርት እንወስደዋለን፡፡
- በሰርቨርና ኮምፒውተር እና እስካነር የፍራንክፈርት ኢምባሲ ስለሆነ የምናጣራ ይሆናል፡፡
- ቁጥር 938/የፍጥነት መቆጣጠሪያ/ የሚያሳየው የተመለሰ የገንዘብ ምዝገባ ነው
- የችግኝ ተከላና ከነችግኙ አገልግሎት በ6244 የመሠረተ ልማት እድሳት ስለሚል ነው ነገር ግን በኦዲት የተሠጠው አስተያየት ትክክል ነው በ6221 በጀት ባለመያዙ የተፈጠረ ነው፡፡

1.4 ግኝት የወጪውን ትክክለኛነት ማረጋገጥ ያልተቻለ ክፍያ ብር 24,957.00

የፌደራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 ክፍል 2 ቁጥር 14/4 ክፍያ ለሚፈፀምባቸው ወጪዎች ተገቢው የሰነድ ማስረጃ መሟላት እንዳለበት ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ በኤጀንሲው የሚፈፀሙ ክፍያዎች ተገቢው ማስረጃ ቀርቦላቸው በወጪ የሚመዘገቡ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በኢንቮይስ ቁጥር 1956 በቀን 29/10/13 በሂሳብ መደብ 2241106 (6256) በሂሳብ እንቅስቃሴ መዝገብ በወጪ ከሚታየው ብር 134,906.81 ውስጥ በዱባይ ኤምባሲ በወጪ ማስመስከሪያ ቁጥር 000328 ለብር 24,957.00 የቀረበው ማስረጃ ትክክለኛና ህጋዊ ስለመሆኑ ማረጋገጥ አልተቻለም፡፡

ስጋት፤

- ክፍያው ለመ/ቤቱ አገልግሎት ላይውል ይችላል፡፡
- የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብና በኦዲት ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም መ/ቤቱ ክፍያ ሲፈፅም የተሟላና ትክክለኛ ማስረጃ ስለመቅረቡ ሊያረጋግጥ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ

ብር 24,957 በተመለከተ በዱባይ ኢምባሲ በወጪ ማስመስከሪያ 328 በቂ ማስረጃ ያልቀረበበትን ምክንያት የምናጣራ ይሆናል፡፡

የኦዲተሩ አስተያየት፤

በተሰጠው ምላሽ መሰረት የማስረጃው ትክክለኛነት ተጣርቶ ለኦዲቱ እንዲቀርብ መደረግ ይኖርበታል፡፡

1.5 ግኝት ማስረጃ ሳይቀርብ በወጪ የተመዘገበ በድምሩ ብር 53,648.21

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ክፍል 2 ተራ ቁጥር 8(2/ለ) የወጪ ሂሳብ ወጪ ከመደረጉ በፊት ስለ ወጪው የተሟላ ማስራጃ መቅረብ እንደሚገባ ያዛል፡፡ ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በመመሪያው መሰረት ክፍያ የሚፈፅም መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤ በተለያዩ ቀናትና የወጪ ማስመሰከሪያዎች በድምሩ ብር 53,648.21 የወጪ ማስረጃ ሳይኖረው ወጪ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ስጋት፤

የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ወጪዎች ሊመዘገቡና የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ፤

ማስረጃዎች ቀርቧል ቢባልም ለኦዲት ስራ አልቀረበም፡፡ በመሆኑም ተገቢው ማስረጃ ሊቀርብ ወይም ገንዘቡ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል ፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

- ብር 51,614.82 ሠነዱ ተሟልቷል፡፡
- ብር 303,640.45 ሳይሆን የነበረበት 309,499.69 ነው ነገር ግን መመዝገብ የነበበረበት በሂሳብ አርስ (6254) በስህተት(6256) ተመዝግቧል
- ብር 158,853.10 ለሥራ አመራር የተከፈለና የተወራረደ ነው
- ብር 134,048.46 በተመለከተ የምናጣራ ይሆናል፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት</u>

ከመውጫ ስብሰባ በኃላ ከብር 51,614.82 ውስጥ ብር 39,665.41 ማስረጃ ቀርቦ የተረጋገጠ ሲሆን ቀሪው ብር 11,949.41 ማስረጃ አልቀረበለትም፤፡ በተጨማሪም ብር 18,329.24 እንዲሁም ብር 23,369.56 ማስረጃ አልቀረበላቸውም፡፡ በመሆኑም በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት ለብር 53,648.21 ማስረጃዎቹ ሊቀርቡ ወይም ገንዘቡ ከሚመለከታቸው አካላት ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

1.6 <u>ግኝት የንብረት ገቢ ደረሰኝ/ሞ19/ ያልተቀረጠለት ብር 819,568.97</u>

በፌዴራል መንግስት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 አንቀፅ 9 ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት ሊደረግ የሚገባው ጥንቃቄዎች በሚለው ስር ንዑስ አንቀፅ 3 ማንኛውም ክፍያ ከመፈፀሙ በፊት የተገዛው ዕቃው ወደ ኤጀንሲው ዕቃ ግምጃ ቤት ለመግባቱ የዕቃ ገቢ ደረሰኝ መቅረቡ መረጋገጥ እንደሚገባ ይገልጻል፡፡ ነገር ግን በተለያዩ ቀናትና የወጪ

ማስመስከሪያ ቁጥሮች በድምሩ ብር 819,568.97 ለተገዙ ንብረቶች የንብረት ገቢ ሞ-19 ሳይቀረጥ በወጪ ተመዝግቦ ተገኝቷል፡፡

<u>ስጋት፤</u>

- የመንግስት ገንዘብ ለብክነት ሊዳረግ ይችላል፡፡
- ንብረቱ ለመ/ቤቱ አገልግሎት ላይውል ይችላል፡፡
- ገቢ ላልተደረጉ ንብረቶች ክፍያ መፈፀሙ ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

<u>የማሻሻያ ሃሳብ፤</u>

ንብረቱ ለመ/ቤቱ አገልግሎት ለመዋሉ ማረጋገጫ እንዲቀርብ ወይም ገንዘቡ ከሚመለከተው አካል ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱ ኤጀንሲው ማንኛውንም ክፍያ ሲፈፅም የመንግስትን መመሪያ ሊከተል ይገባዋል፡፡

<u>የስራ አመራሩ ምላሽ</u>

ከተራ ቁጥር 1-9 ድረስ የተዘረዘሩት የኦዲት ግኝቶች የውጪ ሀገር ሚሲዮን የተላከ ሰነድ በመሆኑ የዱባይ ፣ ፍራንክፈርት ደብዳቤ በመላክ የምናጣራ ይሆናል፡፡

<u>የኦዲተሩ አስተያየት፤</u>

በተሰጠው ምላሽ መሰረት ሁኔታው ተጣርቶ ንብረቶቹ ገቢ መደረጋቸው ሊረጋገጥ ይገባል፡፡

2. **<u>ተሰብሳቢ ሂሳብ፤</u>**

2.1 **<u>ግኝት፤ በወቅቱ ያልተወራረደ ተሰብሳቢ ሂሳብ ብር 93,724,513.87</u>**

በሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር 190/2002 አንቀጽ 32 ፣ የፌደራል መንግሥት ገንዘብ ክፍያ መመሪያ ቁጥር 4/2003 እንዲሁም በፌዴራል የመንግሥት መሥሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 መሰረት ቅድሚያ ክፍያዎች በወቅቱ የሚወራረዱ መሆኑን ለማጣራት ኦዲት ሲደረግ፤

በኤጀንሲው የሰኔ 30/2013 የሂሳብ ሪፖርት ላይ በሂሳብ መደብ 5217109 (4210) ብር 93,010,204.16 ለ36 በውጪ ሀገራት ለሚገኙ ኢንባሲዎችና ቆንጽላ ጽ/ቤቶች የተላከ ሲሆን በዕድሜ ተተንትኖ ያልቀረበና በወቅቱ ያልተወራረደ፣ በሂሳብ መደብ 5217112/አዲስ/ ብር 170,997.84 አንድ ዓመት የሆነውና ያልተወራረደ፣ በሂሳብ መደብ 5217205/4253/ ብር 467,966.25 ከ1 ዓመት በላይ የሆነና ያልተወራረደ እንዲሁም በሂሳብ መደብ 5217302/4202/ ብር 75,345.62 ከ0 እስከ 1 ዓመት የሆነውና ተመላሽ ያልተደረገ በድምሩ ብር **93,724,513.87** የቆየ እና በወቅቱ ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩ በኦዲቱ ወቅት ለማረጋገጥ ተችሏል።

<u>ስጋት፤</u>

- በተሰብሳቢ ሂሳቦች ላይ ተገቢውን ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ የመንግሥት ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊቀር ወይም ለብክነት ሊዳረግ ይችላል።
- ውዝፍ ተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት እንዲኖር ሊያደርግ ይችላል።

<u>የማሻሻ ሃሳብ፤</u>

የሂሳብ መደብ 5217109 (4210) በሚመለከት በባለፈው ዓመት ጋር ሲነጻጸር በብር 93,010,204.16 - 63,171,639.12/ **29,838,565.04** የተሰብሳቢ ሂሳቡ የጨመረ ሲሆን በኮቪድ ምክንያት ጥቅም ላይ ያልዋለ ከሆነ በጀቱን በመጠቀም የዘንድሮ ዓመት ተሰብሳቢ ሂሳብ መቀነስ እንጂ ሊጨምር አይገባውም በመሆኑም የተሰብሳቢ ሂሳቡ በአግባቡ ከውጭ ጉዳይ ሚ/ር ጋር በመናበብ ተገቢ ማስረጃዎች ቀርቦ ሊወራረድ ይገባል፡፡ ቀሪዎቹም መነሻቸው ውል ነው ቢባልም ውሉ ላይ በምን ያህል ግዜ እቃውን ወይም አገልግሎቱ ሊቀርብ እንደሚችል በግልጽ የተቀመጠ ነገር የለም ቀሪዎቹም የተሰብሳቢ ሂሳቦች ማስረጃ

ቀርቦላቸው እንዲወራረዱ እንዲሁም ተመላሽ ሊደረጉ የሚገባቸው ተመላሽ እንዲደረጉ ተገቢው ክትትል ሊደረግ ይገባል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ፤

- ብር 93,010,204.16 በተመለከተ በውጪ ሀገር ለሚኖሩ 36 ሚሲዮኖች ለስራ ማስኬጃ የተላከ ገንዘብ ሲሆን አብዛኛው በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት በስራ ላይ ባለመዋሉ ገንዘቡ ሊወራረድ አልቻለም፡፡
- ብር 170,997.84 በተመለከተ የውጭ ሀገራት የህግ ከለላ ዳይሬክሬት በሳውዲ አረቢያ በመሄድ ወቅቱ የሂሳብ መዝጊያ በመሆኑና እዚያው በመቆየታቸው ምክንያት አልተወራረደም ነገር ግን በ2014 ተወራርዷል፡፡
- ብር 1,195,966.25 በተመለከተ የህንጻ ኪራይ የህንጻ ዋስትና በውሉ መሠረት የተከፈለ ቅድመ ክፍያ ሲሆን ሌላው ለ2014 የኤጀንሲው ካሌንደርና የተለያዩ ህትመት ውጤቶች ቅድመ ክፍያና ለኢትዮጵያ ዜና አገልግሎት ወቅታዊ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ በተሠጠው አቅጣጫ መሠረት ለዶክመንተሪ ፊልም ለማዘጋጀት የተከፈለ፤
- ብር 75,345.62 በተመለከተ በ2013 በጀት ዓመት ሐምሌ 27/2012 ዓ.ም በገንዘብ ቤት ላይ በደረሠው ስርቆት ወንጀል ምክንያት ጉዳዩ በፖሊስ የተያዘ መሆኑን

የኦዲተሩ አስተያየት፤

- ለ36 ሚሲዮኖች ለስራ ማስኬጃ የተላከው ብር 93,010,204.16 አብዛኛው በኮቪድ 19 ወረርሽኝ ምክንያት በስራ ላይ አለመዋሉ ቢገለፅም ያልተሰራበት ገንዘብ ተመላሽ ተደርጉ ሂሳቡ ከተሰብሳቢ እንዲሰረዝ እንዲሁም በስራ ላይ የዋለው ማስረጃ ቀርቦ መወራረድ ሲገባው ምንም እርምጃ ሳይወሰድ ተገኝቷል፡፡
- በጥሬ ገንዘብ ጉድለት የታየው ብር 75,345.62 ክትትል ተደርጎ ገንዘቡ ከሚመለከተው አካል ወይም ሰራተኛ ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡

በአጠቃላይ በተሰብሳቢ የተያዘው ሂሳብ በተሰጠው የማሻሻያ ሀሳብ መሰረት ማስረጃ ቀርቦ እንዲወራረድ ወይም ገንዘቡ ገቢ እንዲደረግ ክትትል መደረግ ይኖርበታል፡፡

3. በጀት፤

3.1 ግኝት ሥራ ላይ ያልዋለ በጀት ብር 83,706,611.11

የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል 3 አንቀጽ 02/1 መሰረት መ/ቤቱ ለበጀት ዓመቱ የተፈቀደለትን የመደበኛ በጀት አጠቃቀም በሚገባ መቆጣጠሩን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

ኤጀንሲው በበጀት ዓመቱ በተለያዩ የሂሳብ መደቦች ከተመደበው መደበኛ በጀት ከ10% በላይ በበጀት አመቱ በየሂሳብ መደቦቹ ከብር **122,432,153.00 ውስጥ** *ሥራ ላይ* የዋለው ብር **38,725,541.89** ሲሆን ብር **83,706,611.11** (68.37%) ያልተሰራበት በጀት መሆኑ ታውቋል፡፡

ስጋት፤

በጀቱ በዕቅዱ መሰረት ስራ ላይ እንዲውል አለመደረጉ የኤጀንሲውን አመታዊ የስራ ውጤት ዝቅ የሚያደርግ ከመሆኑም በተጨማሪ የበጀት ዕቅዱን ትክክለኛነት ላያመለክት ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በእቅድና በፕሮግራም ላይ የተመሰረተ በጀት ሊያዝ ይገባል፡፡ እንዲሁም ኤጀንሲው የተፈቀደለትን በጀት በአግባቡ ስራ ላይ ለማዋል እንዲችል በበጀት አጠቃቀምና አፈፃፀም ላይ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር መደረግ ይኖርበታል፡፡

የስራ አመራሩ ምላሽ፤

በ2013 በጀት አመት በሂሳብ መደብ 6111 የ5 ሰራተኞች ቅጥር ፤የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ፣የኮምፕዩተር ጥገናና ቴክንሽያን፣የመረጃና ጥናት ባለሙያ፣የእቅድ ዝግጅተና ግምገማ ባለሙያ፣የሒሳብ ሰነድ ያዥ- ለመቅጠር የተያዘው አለመከናወን፣

6121 - ለኤጀንሲው ዋና ዳይሬክቴር የተያዘ ዉሎ አበል ሆኖ በበጀት አመቱ ከተወሰነ ወራት ቦኃላ በመንግሰት ቤት ስለተሰጣቸው ውሎ አበሉ እንዲቋረጥ በመደረጉ

6131 - በእቅድ የተያዘው ቅጥር ባለመከናወኑ

6212 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 1,000,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች ስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ በለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6213 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 300,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች ስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት

የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ በለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6217 - በበ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 1,000,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች ስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ በለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6218 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 500,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች ስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ በለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6219 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 700,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች ስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ በለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ

6231 -_በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 9,300,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች የስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.ና Outreach ፕሮግራም የታቀደው መሰረት በኮቪድ ምክንያት ሳይካሄድ በመቅረቱ

6232 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 1,000,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች የስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.ና Outreach ፕሮግራም የታቀደው መሰረት በኮቪድ ምክንያት ሳይካሄድ በመቅረቱ

6233 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 4,000,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች የስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6241 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 300,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች የስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6243 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 400,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች የስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6251 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 2000,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች የስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6253 - የአየር ስዓት በመግዛት በቲቭ የዳያስፖራ እንቅስቃሴ ፕሮግረም ለመስራት የታቀደው በተዳጋጋሚ ተወዳዳሪ ሚዲያዎችን ጨረታ ቢወጣም በቂ ተወዳዳሪ ለማግኘት ባለመቻሉ በጀቱ ስራ ላይ አልዋለም፡፡በመሆኑ 5,000,000.00 ብር ለ35 ሚሲዮኖች መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ አለማዋላቸው ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6254 - ይህ የሂሳብ መደብ በበጀት አመቱ በውጭ የዳያስፖራ ስራዎችን ለሚሰሩ ዲፕሎማቶች ለጤና ኢንሹራንስ ወጪ የተያዘ በጀት ሲሆን ወደ ውጭ ጉዳይ ሚ/ር ሽግሽግ የሚደረግ በጀት ሆኖ ሳለ በ1ኛ ሩብ አመት 2,963,197 ብር Disbursement ተጠይቆበት ወደ ኤጀንሲው በመምጣቱ አና የገንዘብ ሚኒስቴር disburse የሆነውን ግምት ውስጥ ሳይገባ ዝውውር በመስራቱ የበጀት አመቱ በጀት negative በመሆኑ negative በጀቱን ለማስተካክ ከሚ/ሩ ጋር በመነጋገር ተጨማሪ በጀት ተጠይቆ በሂሳብ መደቡ ላይ የተቀመጠ በጀት ነው፡፡

6255 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 200,000 ብር ለ35 ሚሲዮኖች ስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6256 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 4,000,000 ብር ለ35 ሚሲዮኖች የስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6258 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 2,000,000 ብር ለ35 ሚሲዮኖች የስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

6259 - በ3ኛ እና 4ኛ ሩብ አመት 300,000 ብር ለ35 ሚሲዮኖች የስራ ማስኬጃ መላክ የነበረበት ሚሲዮኖች በ2012 በጀት አመትና በ2013 በጀት አመት በ1ኛ እና 2ኛ ሩብ አመት የተላከላቸው ገንዘብ በኮቪድ-19 ምክንያት ስራ ላይ ባለማዋላቸው ምክንያት ወደ መንግስት ግምጃ ቤት እንዲመለስ መደረጉ.

3.2 ግኝት አለአግባብ የተፈጸመ የበጀት ዝውውር

የፌደራል መንግስት የበጀት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 2/2003 ክፍል አራት ተራ ቁጥር 13 የበጀት ዝውውር ስልጣን ውክልና ሚኒስቴሩ በፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ ቁጥር 648/2001 አንቀጽ

24(2) መሰረት የተሰጠውን የበጀት ዝውውር ስልጣን በውክልና ለመንግስት መስሪያ ቤቶች የበላይ ኃላፊዎች መሆን እንደሚገባ እና በተራ ቁጥር 18 ላይ ዉክልና የተሰጠው የበላይ ኃላፊው በሚወክለው ሰው የበጀት ዝውውሩ ቅጽ በትክክልና በበቂ ኮፒዎች መሞላቱን ካረጋገጠ በኋላ ስለ ገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ሚኒስቴር በሚለው ክፍት ቦታ ላይ መፈረም እንደሚችል ይገልጻል ይሁን እንጂ በድምሩ ብር 7,050,000.00 ያለ ውክልና በከፍተኛ የዕቅድ ዝግጅት ግምገማ ባለሙያ ተከናውኖ ተገኝቷል፤

በተጨማሪ በዚሁ መመሪያ ተራ ቁጥር 2 ላይ ከአንድ ዋና የሂሳብ መደብ ወደ ሌላ ዋና የሂሳብ መደብ ከ6400/ለድጋፍና ለመዋጮ /ከተፈቀደው በጀት ወደ ሌላ እንዲሁም ከ 6100 /ከደመወዝና አበል /ወደ 6200 /ስራ ማስኬጃ /በጀት ማዛወር በሚፈለግበት ጊዜ የበጀት ዝውውር ጥያቄን ለሚኒስቴሩ ቀርቦ መፈቀድ እንዳለበት ያዛል ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በከፍተኛ የዕቅድ ዝግጅት ግምገማ ባለሙያ ከመመሪያው ውጪ የብር 3,600,000.00 ለገንዘብ ሚንስቴር ሳይቀርብ ዝውውር የተፈጸመ መሆኑን ለማወቅ ተችሏል ፡፡

ስጋት

- የበጀት አጠቃቀሙን መመሪያ መሰረት ያላደረገ ከሆነ ለዚሁ ተብሎ የተዘረጋውን የቁጥጥር ስርዓት እንዲጣስ ሊያደርግ ይችላል፡፡
- ከመመሪያና ከተሰጣቸው ውክልና ውጭ የበጀት ዝውውር ሊከናወን ይችላል፡፡
- ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ

በመመሪያው መሰረት መ/ቤቱ የበጀት ዝውውር ጥያቄውን ለገንዘብ ሚንስቴር ቀርቦ ማስፈቀድ ሲገባው ሳይፈቀድ የሚዘዋወር በጀት ለብክነት የሚዳርግና መመሪያዎች አለማክበር የበጀት ዝውውር ውክልናን እስከማንሳት የሚያስከትል በመሆኑ አሰራሩ ሊስተካከል ይገባል፡፡ በመሆኑም ኤጀንሲው የበጀት ዝውውሮችን በበጀት አስተዳደር መመሪያ መሰረት ሊያከናውን ይገባል::

የስራ አመራሩ ምላሽ

በአዲሱ በኢፍሚስ ሴስተም የተቋሙን በጀት ዝውውር ማፅደቅ እሚችለው ሁለት አካላት ሲሆኑ እነሱም (top management) ወይም (planning case team leader) ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ከላይ በዝርዝሩ የቀረቡ የበጀት ዝውውር ከ(top management) ወ/ሮ ሰላማዊት ዳዊት ጋር በመነጋገር የተፈፀመ ሲሆን በወቅቱ የወ/ሮ ሰላማዊት ዳዊት የኢፍሚስ የይለፍ ቁጥር (Passward) ባለመጠቀማቸው ምክንያት ባለመከፈቱ እና ይህንን ለሚመለከተው ክፍል በማሳወቅ እና ሲስተም ከሁለቱ አንዱ ካፀደቀ ስለሚቀበል የተከናወነ ነው፡፡

4. ንብረትን በተመለከተ፤

4.1 ግኝት በንብረት አያያዝ አጠባበቅን በሚመለከት

የኤጀንሲው የንብረት አስተዳደር በፌደራል መንግስት የንብረት አስተዳደር መመሪያ ቁጥር 9/2003 መሰረት የሚከናወን መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፤

በክፍል 3 የስቶክ አስተዳደር ስርአት ተራ ቁጥር 11 /1 የመንግስት መ/ቤቶች ኤጀንሲው ባዘጋጃቸው ቅጾች መሰረት የስቶክ መረጃዎችን መያዝ እንዳለባቸው ያዛል ይሁን እንጂ ኤጀንሲው በተለያየ ጊዜ ለስራ የሚያስፈልጋቸውን ቋሚ ንብረቶች ተገዝተው ገቢ መሆናቸውን በናሙና ኦዲት በምናደርግበት ጊዜ

- ሲሪያል ቁጥር ያላቸው ንብረቶች ተገዝተው በሞዴል 19 (የንብረት ገቢ ደረሰኝ) እንዲሁም በሞዴል22 (የንብረት ወጪ ደረሰኝ) ተጠይቆ በሁለቱም ገቢም ሆነ ወጪ ሲደረጉ የተመረተበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) የማይመዘገብ መሆኑ
- በክፍል 3 የስቶክ አስተዳደር ስርአት ተራ ቁጥር 10 ሀ የስቶክ መዛግብቶች የመያዝና የመረከብ እንዲሁም ወጪ የማድረግ ኃላፊነቶች ለአንድ ሰራተኛ መሰጠት እንደሌለባቸው ያዛል የሁን እንጂ በኤጀንሲው የንብረት ክፍል መዝጋቢ እና የንብረት ጠባቂ ያልተለየ እና በአንድ ሰው ብቻ የሚፈጸም መሆኑን፤
- በክፍል 3 የስቶክ አስተዳደር ስርአት ተራ ቁጥር 9 የስቶክ ቁጥትር ስርአቶች ተራ ቁ.2/ሐ ንብረት ገቢ ወይም ወጪ ከተደረገባቸው በኋላ በተቻለ ፍጥነት ዋናው የስቶክ መዛግብቶች ላይ ማሻሻያ መደረግ እንዳለበት ያዛል ነገር ግን በ/መ/ቤቱ የስቶክ ካርድ በአገልግሎት ላይ አለመዋሉን በኦዲቱ ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

ስጋት፤

- በተመረተበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) ካልተመዘገቡ በቀላሉ ሊቀየሩና ለቁጥጥር አመቺ ላይሆን ይችላል፡፡
- መ/ቤቱ መንግስት ባወጣው የንብረት አስተዳደር መመሪያና ደንብ መሰረት የማይፈጽም ከሆነ ለውስጥ ቁጥጥር ስርአት መዳከም ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

የማሻሻያ ሃሳብ፤

- ሲሪያል ቁጥር ያላቸው አይተሞች ኢፍሚስ ስስተም ላይ ማስገባት የሚቻል በመሆኑ ምላሹን አልተቀበልነውም በመሆኑም በመመሪያው መሠረት የመንግስት ቋሚ ንብረቶች ተገዝተው እንደመጡ ሂሳቡ ከመወራረዱ በፊት (የንብረት ገቢ ደረሰኝ) እንዲሁም በሞዴል20 (የንብረት ወጪ ደረሰኝ) ተጠይቆ በሁለቱም ገቢም ሆነ ወጪ ሲደረጉ የተመረተበት የፋብሪካ ቁጥር (ሴሪ ቁጥር) ተመሳክሮ ሊመዘገብ ይገባል::
- በመመሪያው መሰረት ንብረቶች ከቢን ካርድ ቀጥሎ በእስቶክ ካርድ ላይ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡
- ንብረት የመመዝገብና የመጠበቅ ስራ በተለያዩ ሰዎች ሊከናወን ይገባል::

የስራ አመራሩ ምላሽ

ምንም እንኳን በኦዲተሩ የተሠጠው አስተያየት ትክክለኛ ቢሆንም በተቻለ መጠን ህግና ስርዓት ተከትሎ ለመስራት ጥረት እያደረግን መሆኑንና ኤጀንሲው አዲስ እንደመሆኑና መዋቅራዊ ስትራክቸር ችግሮች ቢኖሩትም ባለው የሠው ሀይል በመስራትና ባለው ክፍተት ባለሙያ ተቀጥረው ወደ ሲስተም እንዳይገባ ስልጠና ያስፈልገዋል መዝጋቢና ተረካቢ አሁን ላይ ተለይቷል በመሆኑም ቢን ካርድ ተዘጋጅቷል ንብረቱንም በተመለከተ በሞዴል 19 ገቢ እየሆነ በሞዴል 20 ወጪ እያደረግን ነው ነገር ግን IFIMIS ሲሪያል ቁጥር የለውም

<u>**የኦዲተሩ አስተያየት**</u>

በተሰጠው የማሻሻያ ሃሳብ መሰረት ለወደፊቱ ማስተካከያ ሊደረግ ይገባል፡፡

5. <u>የክትትል ኦዲት፤</u>

- በስቶር ውስጥ የእሳት አደጋ መከላከያ/እሳት ማጥፍያ (Fire Extinguisher) የሌለ መሆኑ፤

በመጨረሻ በኦዲቱ ወቅት ለተደረገልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡